# በመጽሐፍ ቅዱስ የአፈታት ጥበብ ረገድ የቺካጎ የእምነት መግለጫ

**(ርዕስ ቁ 2)**

የቅጂ መብት 1978 አይሲቢአይ፣ መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው፡፡ የአይሲቢአይ መዝገብ ማከማቻ ከሆነው የዲሊስ ቲዎልጂካሌ ሴሚናሪ መዝገብ ቤት በፈቃድ የታተመ

**አንቀጽ I.**

- የቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ሥልጣን የእግዚአብሔር የራሱ ሥልጣን እንደሆነና ይህንንም የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳረጋገጠው **እናምናለን።**
- ነገር ግን የክርስቶስን ሥልጣን ከእግዚአብሔር ቃል ሥልጣን የመለየትን አግባብ ወይም አንዱ የሌላው ተቃራኒ መሆኑን **አናምንም፡፡**

**አንቀጽ II.**

- ክርስቶስም በአንድ ማንነት አምላክ እና ሰው እንደሆነ ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስም በሰው ቋንቋ የተጻፈ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ **እናምናለን።**
- ክርስቶስ ራሱን ባዋረደበት ጊዜ እንኳን ኃጢአት እንዳደረበት እንደማናምን ሁሉ የእግዚአብሔር ቃል ዝቅ ባለ ደረጃ በሰው ቋንቋ የተጻፈው መሆኑ የተነሳ ስህተት እንዳለበት **አናምንም።**

**አንቀጽ III.**

- የኢየሱስ ክርስቶስ ማንነትና ስራ የመላው መጽሐፍ ቅዱስ ማእከላዊ አትኩሮት እንደሆነ **እናምናለን።**
- ነገር ግን የክርስቶስን ማዕከላዊነት በማይቀበል ወይም ግልጽ እንዳይሆን በሚያደርግ የአተረጓጎም መንገድ **አናምንም።**

**አንቀጽ IV**

- የእግዚአብሔር ቃል እንዲጻፍ ያደረገው መንፈስ ቅዱስ በዚሁ ቃል አማካይነት በሚተላለፈው መልዕክት ዛሬም እምነትን ለመፍጠር እንደሚሰራ **እናምናለን፡፡**
- ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚጣረስ ነገር ለማንም ምንም እንደሚያስተምር **እናምንም።**

**አንቀጽ V**

- መንፈስ ቅዱስ አማኞች በእግዚአብሔር ቃል እንዲታነጹና በሕይወታቸው እንዲተገብሩት ኃይል እንደሚሰጣቸው **እናምናለን።**
- ነገር ግን ተፈጥሮአዊው ሰው መጽሐፍ ቅዱሳዊውን መልዕክት መንፈሳዊ መለከት ያለ መንፈስ ቅዱስ ሊረዳው እንደሚችል **አናምንም።**

**አንቀጽ VI**

- መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን እውነት በጽሑፍ እንደገለጸው(እንዳሰፈረው) እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱሳዊው እውነት ነባራዊና ፍጹም እንደሆነ እናምናለን፡፡ ከዚህ በተጨማሪም አንድ ዐረፍተ ነገር (አባባል) እውን የሆነን ነገር የሚወክል ከሆነ እውነት እንደሆነ እናምናለን፤ ይሁንና እውነታን (እውን የሆነን ነገር) የማይወክል ከሆነ ሐሰት እንደሆነ **እናምናለን።**
- የእግዚአብሔር ቃል ለድነት ጥበበኛ ሊያደርገን የሚችል ሆኖ ሳለ መጽሐፍ ቅዱሳዊው እውነት ከዚህ ተግባር አኳያ ብቻ መተርጎም አለበት በሚለው አባባል አናምንም። ከዚህ በተጨማሪም ስህተት ማለት መተርጎም ያለበት ሆን ብሎ ማሳሳት ከሚለው አኳያ ብቻ እንደሆነ **አናምንም።**

**አንቀጽ VII**

- በእያንዳንዱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንባብ ውስጥ ያለው ትርጉም (ፍቺ) አንድ፣ የታወቀና የተወሰነ እንደሆነ **እናምናለን፡፡**

- አንድ ትርጉም ብቻ ነው ያለው የሚለው አቋም በብዙ መንገዶች ማዛመድን ያግዳል ብለን **እናምንም።**

**አንቀጽ VIII**

- መጽሐፍ ቅዱስ በዓለም ባህላዊና ሁኔታዊው አውዶች ውስጥ የሚተገበሩ አስተምህሮዎችንና ኃላፊነቶችን እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ በልዩ ሁኔታዎች ውስጥ ብቻ እንዲተገበሩ የሚያሳያቸውን ኃላፊነቶች እንደያዘ **እናምናለን።**
- በእግዚአብሔር ቃል ዓለም አቀፋዊና ልዩ ኃላፊነቶች መካከል ያለው ልዩነት የሚወሰነው በባህልና ሁኔታዊ ምክንያቶች ነው በሚለው **እናምንም።** በተጨማሪም ዓለም አቀፋዊ ኃላፊነቶች ባሕላዊ አንጻራዊነት እንዳላቸው **እናምንም።**

**አንቀጽ IX**

- በታሪክ የሐቲት መመሪያ ተብሎ የሚታወቀው የመጽሐፍ ቅዱስ ስነ አፈታት (የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም) የመጽሀፍ ቅዱስሳዊውን መገለጥ ምንነትና ለሕይወታችን የሚሰጠውን ጥቅም በመረዳት ሂደት ውስጥ ያለውን ሁሉ ለመሸፈን በተገቢው መንገድ ጥቅም ላይ ለማዋል እንደሚቻል **እናምናለን።**
- ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል መልዕክቶች ከተርጓሚው እንደሚመነጭ ወይም በተርጓሚው እንደሚወሰን አናምንም፤ ስለሆነም በስተመጨረሻ ምንባቡ ለተርጓሚው ያስተላለፈው መልእክት በእግዜብሔር ቃል በተገለጸው ትርጉም የተገደበ ሳይሆን የቅዱሳት መጻሕፍት ጸሀፊውና የተርጓሚው አድማሶች በዚህ መንገድ በትክክል ሲዋሃዱ ነው ብለን **አናምንም።**

**አንቀጽ X**

- የእግዚአብሔር ቃል በብዙና በተለያዩ ሥነ - ጽሑፋዊ ቅርጾች አማካይነት የእግዚአብሔር እውነት በቃል ለኛ እንደሚያስተላልፍ **እናምናለን።**
- ማንኛውም የሰብአዊ ቋንቋ ውሱንነት የእግዚአብሔርን መልዕክት በበቂ ሁኔታ ለማስተላለፍ እንዳይችል እንደሚያደርገው **አናምንም።**

**አንቀጽ XI**

- የቅዱሳት መጻሕፍት ምንባብ ትርጉሞች ጊዜያዊና ባህላዊ ገደቦችን አልፎ እግዚአብሔርን የማወቅ መልእክ ሊያስተላልፍ እንደሚችል **እናምናለን።**
- ያንኑ ተመሳሳይ ትርጉም በሌሎች ባህሎች ውስጥ መረዳት እስከማይቻል ድረስ የመጽሀፍ ቅዱስ ምንባብ ትርጉም ከመጣበት ባህል ጋር የተቆራኘ ነው በሚለው **አናምንም።**

**አንቀጽ XII**

- መጽሐፍ ቅዱስን በመተርጎምና በየ ባሕሉ በማስተማር ተግባር ጥቅም ላይ መዋል ያለባቸው ያለባቸው ለመጽሐፍ ቅዱሳዊው ትምህርት ይዘት ታማኝና አቻ የሆኑት ብቻ  እንደሆኑ **እናምናለን፡፡**
- ለባህል ዘለል ተግባቦት ባይተዋር በሆኑ ወይም በአተረጓጎም ሂደት መጽሐፍ ቅዱሳዊው ትርጉምን በሚያዛቡ ሥነ ዘዴዎች **አናምንም።**

**አንቀጽ XIII**

- በተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ መደበኛና ልዩ ልዩ ስነ ጽሑፋዊ መደቦች ተገቢ ለሆነ ሐቲታዊ ተግባር አስፈላጊ እንደሆነና በዚህም ምክንያት በስነ ጽሑፋዊው ቅርጽ ላይ የሚደረገው ሒስ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ የጥናት ዘርፎች አንዱ እንደሆነ **እናምናለን።**
- ታሪካዊነትን የሚጻረሩ ስነ ጽሑፋዊ መደቦች ራሳቸውን እንደ እውነታ በሚያቀርቡ የመጽሐፍ ቅዱሳ ትረካዎች ላይ በመጫን ትክክል ሊሆኑ ይችላሉ ብለን **አናምንም።**

**አንቀጽ XIV**

- በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተዘገቡት ድርጊቶች፣ ገለጻዎችንና አባባሎች ምንም እንኳን ተገቢ በሆኑ ሥነ - ጽሑፋዊ ቅርጾች የቀረቡ ቢሆኑም ከታሪካዊ እውነታዎች ጋር አንድ እንደሆኑ (አቻ እንደሆኑ ) **እናምናለን።**
- በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የተዘገቡ ማንኛውም ድርጊቶችና ገለጻዎች ወይም አባባሎች በቅዱሳት መጽሐፍት ጸሐፊዎች ወይም ባካተቷቸው ትውፊቶች ውስጥ የተፈጠሩ እንደሆኑ  **አናምንም።**

**አንቀጽ XV**

- መጽሐፍ ቅዱስን እንዳለ ቃል በቃል (በቁሙ)መተርጎም አስፈላጊ እንደሆነ እናምናለን። እንዳለ ቃል በቃል (በቁሙ) መተርጎም ማለት ሰዋሰዊ– ታሪካዊ ሁኔታውን ማገናዘብ ማለት ሲሆን ይህም ጸሐፊው ትርጉሙን የገለጸበት እንደሆነ እናምናለን፡፡ በቁማዊ አጻጻፍ አኳያ የሚደረገው ተግባር በምንባቡ ውስጥ ለሚገኘው ዘይቤአዊ አነጋገሮችና ስነ ጽሑፋዊ ቅርጾች ትኩረት የሚሰጥ እንደሆነ **እናምናለን።**
- መጽሐፍ ቅዱስ ቃል በቃል የማይደግፈውኔን ትርጉም የሚይሰጥ ማንኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ አፈታት ትክክል እንደሆነ **አናምንም።**

**አንቀጽ XVI**

- አግባብነት ያላቸው ሒሳዊ ስልቶች ቀኖናዊ ምንባብንና ትርጉሙን ለመለየት ጥቅም ላይ መዋG እንዳለባቸው **እናምናለን።**
- ነገር ግን እውነትን ወይም ጸሐፊውን የገለጸውኔን ትርጉም ርቱዕነትን ወይም ሌላ ማንኛውንም የእግዚአብሔር ቃል ትምህርትን ጥያቄ ውስጥ በሚያስገባ በማንኛውም የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ሒስ ሥነ ዘዴ **አናምንም።**

**አንቀጽ XVII**

- የእግዚአብሔር ቃል አንድ፣ ስምሙ እና ወጥነት ያለውኔ እንደሆነና ራሱ የራሱ የላቀ ተርጓሚ እንደሆነ **እናምናለን።**
- አንዱ ምንባብ በሌላው ምንባብ ላይ እርማት ማደረጉን ወይም አንዱ በሌላው ላይ አሉቫዊ ተጽእኖ እንዳለው በሚያሳይ መልኩ የእግዚአብሔር ቃል ሊተረጎም ይችላል በሚለው አናምንም፤ የኋለኞቹ የቅዱሳት መጻሕፍት ጸሐፊዎች ከቀደሙት ምንባቦች በሚጠቅሱበት ጊዜ ወይም በሚያመላክቱበት ጊዜ በተሳሳተ መንገድ እንደተረጎሟቸው **አናምንም።**

**አንቀጽ XVIII**

- መጽሐፍ ቅዱስ ስለራሱ ራሱ የሚሰጠው ትርጉም ሁልጊዜ ትክክል እንደሆነና ፍጹም ማፈንገጥ በሌለበት ሁኔታ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበትን ምንባብ ነጠላ ትርጉም እንደሚያብራራው እናምናለን፡፡ አንድ ትርጉም ብቻ ያላቸው የነቢያት ቃሎች በዚሁ ነገር አኳያ የተገደቡ ባይሆኑም ስለ እነዚህ ቃሎች ነቢዩ ያለውን ግንዛቤ የሚያካትትና በእነዚህ ቃሎች መፈጸም የሚረጋገጠውን የእግዚአብሔርን ዓላማ ያካተተም እንደሆነ **እናምናለን፡፡**
- የቅዱሳት መጻሕፍት ጸሐፊዎች የተናገሯቸውን የገዛ ራሳቸውን ቃሎች አንድምታ ሁልጊዜ ይገነዘቡታል ብለን **አናምንም።**

**አንቀጽ XIX**

- ተርጓሚ የእግዚአብሔር ቃልን ሲያጠና የሚኖረው ቅደመ ግንዛቤ ከእግዚአብሔር ቃል ትምህርት ጋር የተስማማና ከእርምት ነጻ ያልሆነ እንደሆነ **እናምናለን፡፡**
- የእግዚአብሔር ቃል ከእርሱ ጋር ከማይስማሙና እንግዳ ከሆኑ ቅድመ ግንዛቤዎች ጋር ማለትም ከተፈጥሮአዊነት፣ ከዝግመተ ለውጥ፣ ከሳይንሳዊነት ከአለማዊው ሰብአዊነት እና ከአንጻራዊነት ጋር እንዲስማማ መደረግ አለበት ብለን **አናምንም።**

**አንቀጽ XX**

- እግዚአብሔር የእውነት ሁሉ ባለቤት እስከሆነ ድረስ በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥና ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ ባሉ ጽሑፎች ውስጥ ያሉ እውነቶች ሁሉ ወጥነት ያላቸው ሕቡር ሲሆኑ መጽሐፍ ቅዱስም ከተፈጥሮ& ከታሪክ ወይም በሌሎች ጉዳዮች ላይ ሲያስተምር እውነትን እንደሚናገር እናምናለን፡፡ በተጨማሪ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ ያሉ መረጃዎች መጽሐፍ ቅዱስ በአንዳንድ ጉዳይ ላይ የሚያስተምረው ለማብረራት ፋይዳ እንዳለቸውና ሐሳዊ ትርጉሞችን ለማረም ፍንጭ እንደሚሰጥ **እናምናለን።**
- ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ የሚገኙ አመለካከቶች ለእግዚአብሔር ቃል ትምህርት ተቃውሞ ማረጋገጫ ሊሰጡ እንደሚችሉ ወይም በእግዚአብሔር ቃል ትምህርቶች ላይ የበላይ ሊሆኑ እንደሚችሉ **አናምንም።**

**አንቀጽ XXI**

- ልዩ መገለጥ ከአጠቃላይ መገለጥ ጋር እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ከተፈጥሮ እውነት ጋር ስምሙ እንደሆነ **እናምናለን።**

- ከየትኛውም የእግዚብሔር ቃል ምንባብ ትርጉም ጋር በማይስማማ (የማይጣጣም) ሳይንሳዊ እውነት **አናምንም።**

**አንቀጽ XXII**

- ዘፍ 1÷11 እንደሌላው መጽሐፍ ሁሉ እውነት እንደሆነ **እናምናለን።**
- ዘፍ 1÷11 ስለ ምድር ታሪክና ስለ ሰው ልጅ አመጣጥ የሚያስተምረው ትምህርት ምናባዊ ፈጠራ እና ሳይንሳዊ መላ ምት እንደሆነ በመቁጠር የእግዚአብሔር ቃል ስለ ፍጥረት የሚያስተምረውን ትምህርት አውጥቶ በመጣል **አናምንም።**

**አንቀጽ XXIII**

- በእግዚአብሔር ቃል ግልጽነት፣ በተለይም ከኃጢአት ስለ መዳን በሚያስተላልፈው መልዕክት **እናምናለን።**
- ሁሉም የእግዚአብሔር ቃል ምንባቦች ስለቤዛነት በሚያስተላልፉት መልዕክት እኩል ግልጽ እንደሆኑ ወይም በእኩልነት እንዳሰፈሩ **አናምንም።**

**አንቀጽ XXIV**

- አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ቃል ለመረዳት በመጽሐፍ ቅዱስ የነገረ መለኮት ምሁራን ክህሎት ላይ ጥገኛ እንዳልሆነ **እናምናለን።**
- አንድ ሰው በመጽሐፍ ቅዱስ የነገረ መለኮት ምሁራን የእግዚአብሔር ቃል የጥናት ውጤቶችን (ፍሬዎችን) ቸል ማለት እንዳለበት **አናምንም፡፡**

**አንቀጽ XXV**

- መለኮታዊ መገለጥንና ትክክለኛ የሕይወት ተዛምዶውን በበቂ ሁኔታ ለማስተላለፍ የሚችል የስብከት ዓይነት የቅዱሳት መጽሕፍትን ምንባብ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ በመቁጠር በታማኝነት ማብራራት የሚችል ብቻ ሲሆን እንደሆነ **እናምናለን።**
- ነገር ግን አንድ ሰባኪ ከእግዚአብሔር ቃል ውጪ መለከት አለው ብለን **አናምንም።**